የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፹፩
አዲስ አበባ ሰኔ ፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No. 81
ADDIS ABABA, 15th June,2016

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፱፻፶፮/፪ሺ፰ ዓ.ም

ለሦስተኛው የአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማስፈጸሚያ አዋጅ ……………………………………………….ገጽ ፱ሺ፩፻

## CONTENT

Proclamation No. 956/2016

International Fund for Agricultural Development Additio Financing Agreement for financing the pastoral commur Development Project III Ratification Proclamation …Page 9100

አዋጅ ቁጥር ፱፻፶፮/፪ሺ፰

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የተጨማሪ በጀት ብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

ለሦስተኛው አርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ፲ ሚሊዮን ፮፻፶ ሺ. ኤስ.ዲ.አር (አስር ሚሊዮን ስድስት መቶ ሃምሳ ሺ. ኤስ.ዲ.አር) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው ተጨማሪ የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ ግብርና ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ ዲሴምበር ፴ ቀን ፪ሺ፲፭ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፳፫ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፣

PROCLAMATION No.956/2016

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE ADDITIONAL FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL FUND FOR AGRICULTURAL DEVELOPMENT**

**WHEREAS**, Additional financing Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the international Fund for Agricultural Development stipulating that the international Fund for Agricultural Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia Additional loan amount of SDR 10,650,000 (ten million six hundred fifty thousand Special Drawing Rights) for financing the pastoral community Development Project III was signed on the 30th day of December 2015;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 31th day of May, 2016;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

በኢትዮጵያ ፌራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡-

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ ”ለሦስተኛው የአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማስፈጸሚያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፶፮/፪ሺ፰” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ ዲሴምበር ፴ ቀን ፪ሺ፲፭ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 2000001396 በዚህ አዋጅ ጸድቋል።

**፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲ ሚሊዮን ፮፻፶ ሺ ኤስ.ዲ.አር (አስር ሚሊዮን ስድስት መቶ ሃምሳ ሺ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሰኔ ፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the ″International Fund for Agricultural Development Additional Financing Agreement for financing the pastoral community Development Project III Ratification Proclamation No. 956/2016″.

**2. Ratification of the Agreement**

The Financing Agreement Number 2000001396 - ET signed on the 30th day of December 2015 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Fund for Agricultural Development is hereby ratified,

**3. Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation**

The Ministry of Finance and Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of SDR 10,650,000 (ten million six hundred fifty thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done of Addis Ababa, this day of 15th June ,2016**

**MULATU TECHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**